# “ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን”

## ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፤

1) በግብርና አገልግሎት ላይ እንዲሁም በግብርና ግብዓትና ምርት ማምረትና ግብይት የሙያ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርት ያዘጋጃል በመስፈርቱም መሰረት ፈቃድ ይሰጣል እንደአስፈላጊነቱያድሳል፤ያግዳል፤ይሰርዛል፡፡

2) በእንስሳት መድኃኒትና መኖ ማምረትና ንግድ ተቋማት ውስጥ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤እንደ አስፈላጊነቱ ያድሳል፤ያግዳል፤ይሰርዛል፡፡

3) የግብርና ግብዓት ወይም ምርት ከውጭ ሀገር ለሚያስገቡ ወይም ለውጪ ሀገር ገበያ ለሚያቀርቡ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ይመዘግባል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፡፡

4) በሀገር ውስጥ ከአንድ ክልል በላይ ለሚደረግ የግብርና ግብዓት እና የግብርና ምርትን ማምረት የግብይት ተግባር ሲኖር የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤ ይመዘግባል፤ ያድሳል፤ያግዳል፤ይሰርዛል፡፡

5) ከውጭ የሚገባና በሀገር ውስጥ የሚበለፅግ የግብርና ቴክኖሎጂ ብቃትን ይፈትሻል ይመዘግባል በአመልካች ሲጠየቅም መርምሮ የአዳቃዮች ባለቤትነት መብት ጥበቃ ይሰጣል ያስተዳድራል፡፡

6) የግብርና ግብዓት እና የግብርና ምርትን ፍቱንነት ጥራት ውጤታማነት ደህንነት በመስፈርቶችና በግብርና ደረጃዎች መሰረት በመገምገም የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

7) የእንስሳት እና የእፅዋት ግብዓት ምርት ማምረቻ፤ማዘጋጃ ማቀናበሪያ፤ ማከማቻ ጅምላ መሸጫ ቦታዎችን በመስፈርት እና በወጡ የግብርና ስታንዳርዶች መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤እንደ አስፈላጊነቱ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፡፡

8) በስራ ላይ ያሉትንና ከግብርና ግብዓት እና የግብርና ምርትን ጥራት ፍቱንነት ደህንነትና ጤንነት ጋር ተያያዥ የሆኑ የግብርና ስታንዳርዶችን ተግባራዊ ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱም ያሻሽላል፤ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበርም አዳዲስ ያወጣል፡፡

9) የግብርና አገልግሎት አሰጣጥን እንዲሁም የግብርና ግብዓትና ምርት አመራረትና ግብይት የሀገሪቱንና እንደአስፈላጊነቱም የአለም አቀፍ የጥራት፤ የኳራንቲን ደህንነትን ስታንዳርዶች አሟልተው እየተከናወኑ መሆኑን በመስክና በላቦራቶሪ ምርመራ ያረጋግጣል ይቆጣጠራል እንደ አስፈላጊነቱም በሌላ አካል እንዲረጋገጥ ያደርጋል እንዲሁም ተቀባይነት ያለው የእፅዋት ወይም የእንስሳት ጤና ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፤

10) በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና ቁጥጥር የሚደረግበት የግብርና ግብዓት እና ምርት በተመለከተ በወጡ የህግ ማዕቀፎች ጥራት ጤንነትና ደህንነት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ የመልቀቂያም ፈቃድ ይሰጣል፤መስፈርቱን ካላሟሉ ያግዳል፤ወይም እንዲታከም ወይም እርምት እንዲደረግበት ወይም አስፈላጊም ከሆነ እንዲወገድ ወይም ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

11) በአገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ሃገር ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ግብዓቶችና ምርቶች በዓለም አቀፍ ወይም በተቀባይ አገር የጥራትና ጤንነትና ደህንነት ስታንዳርድ መሰረት ምርመራ በማካሄድ የምስክር ወረቀት ወይም ዓለም አቀፍ የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ጤና ሠርተፍኬት ይሰጣል፤ ይመዘግባል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

12) በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ባገኘ ሰው በአገር ውስጥ ተመርቶ ወይም ተዘጋጅቶ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ የግብርና ግብዓትና ምርት ባለስልጣኑ ከሚመለከተው ተቋም ጋር በሚያወጣው የጥራትና ጤንነትና ደህንነት ስታንዳርድ መሰረት ምርመራ በማካሄድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይመዘግባል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

13) ዓለም አቀፋዊ ፣አህጉራዊ እና ቀጠናዊ የሬጉላቶሪ እና የኳራንቲን ቁጥጥር መርሆዎች እና ስምምነቶች እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

14) ለግብርና ዓብዓት ምርትና አገልግሎት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንደ አስፈላጊነቱም መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፣ የመረጃን ትክክለኛነትና አግባብነት ያረጋግጣል፣ አሻሚ ወይም ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎች እንዳይሰራጩ ያደርጋል፣

15) የባለስልጣኑ ግብርና ሬጉላቶሪ አገልግሎቶች እንዲቋቋሙ፣ አቅማቸው እንዲገነባና እንደ አስፈላጊነቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን እንዲያገኙ ያደርጋል፣

16) የግብርና ግብዓት ወይም ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝር ተግባራዊ ያደርጋል።በየዓይነታቸው ይመድባል። መዘርዝሮችንም በየጊዜው ይከልሳል። አዳዲሶችንም ያዘጋጃል፡፡

17) የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይና በሽታ እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ የእንስሳት በሽታ ቅኝት፣ አሰሳ እና የስጋት ትንተና ያካሂዳል። የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል። ሥርዓት ይዘረጋል።

18) የዕፅዋትና እንስሳት ኳራንቲን ግልጋሎት የሚሰጥ የቅድመ እና ድህረ መግባት ኳራንቲን እና የዘር-ድህረ ጥራት ቁጥጥር ጣቢያዎች ያቋቁማል። ያደራጃል።

19) የዕፅዋትና እንስሳት ተባይና የበሽታ ስርጭት ጥናት በማድረግ አገራዊ የኳራንታይን ተባይና በሽታ መዘርዝር ያዘጋጃል።

20) የዕፅዋት እና የእንስሳት ግብዓቶች ከተመዘገቡ በኃላ በክምችት በማጓጓዝ፣ በስርጭት፣ በግብይት፣ በአጠቃቀም እና በአወጋገድ ወቅት አግባብነት ባለው የህግ ማዕቀፍ መሰረት ይቆጣጠራል።

21) እንስሳትን እና አንስሳት ውጤት የአንስሳት ተዋጽኦ እና መኖ እንዲሁም ዕጽዋት እና የዕጽዋት ምርት ከሬጉላቶሪ አኳያ ይለያል። ይመዘግባል።አንደ አስፈላጊነቱ የኋላ ታሪክ ያጠናል። ይከታተላል።

22) ባለስልጣኑ በዓለምአቀፍ ደረጃና በሌሎች አገሮች ተቀባይነት ያላቸውን የጋራ ስምምነቶች እና ደረጃዎችንና የሬጉላቶሪ ዘዴዎች አንደ አስፈላጊነቱ ተቀብሎ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል። ለአተገባበራቸውም በህግ መሰረት ይፈራረማል።

23) በዚህ ደንብ ቁጥጥር የሚደረግበት የግብርና ግብዓት ወይም ምርት ይህንን ደንብ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት ሊሟሉ የሚገባቸውን ሳያሟላ ሲቀር እንደአግባቡ ምርቱን ወይም ግብዓቱን ሊይዝ፣ እንዲወገድ ሊያደርግ፣ ከገበያ እንዲሰበሰብ ሊያዝ፣ በህግ አግባብ ሊወርስ ይችላል።

24) በባለስልጣኑ እውቅና ተመዝግቦ ገበያ ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ግብርና ግብዓትና ምርት በሚመለከት ይመረምራል፣ ናሙና ይወስዳል፣ አግባብ ካለው የክልል ባለስልጣን ጋር በመተባበር እርምጃ ይወስዳል።

25) የግብርና ግብዓትና ምርት የሬጉላቶሪ መስፈርት ባለማሟላቱ ምክንያት በአካባቢ፣ በሰው፣ እንስሳት እና በዕጽዋት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደረሰ እንደሆነ ጥናት ያደርጋል፣ ውጤቱን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ አግባብ ካለው የክልል ባለስልጣን ጋር በመተባበር አንዲወሰድ ያደርጋል።

26) የእንስሳት መድኃኒት ወይም ክትባት ፀረ ተባይና ማዳበሪያ ላይ የሚካሄዱ የመስክ ሙከራ ጥያቄዎችን እየመረመረ ይፈቅዳል፣ ሙከራው በመልካም የእንስሳት ህክምና እና ግብርና ሥርዓት መሠረት መካሄዱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል። ምክረ ሃሳብ ያቀርባል። አስፈላጊ ሲሆን ሙከራው እንዲታገድ ወይም እንዲቆም ትእዛዝ ይሰጣል።

27) የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትን፣ ምንጩ ያልታወቀን፣ ከባዕድ ነገር ጋር የተቀላቀለ ወይም መስፈርትን የማያሟላ የግብርና ግብዓት እና ምርት ይወርሳል። መወገድ ያለበትን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገድ ያደርጋል። በአግባቡ መወገዱንም ይቆጣጠራል።

28) ህይወት ያለው ደቂቀ ዘ-አካላት ወይም እንስሳት ወይም እፅዋት ከውጭ ሀገር ሲገባ መርምሮ የመግቢያ ፈቃድ ይሰጣል። የሀገር ውስጥ ብዝሀ ሕይወት ከውጭ በሚገቡ ባዕድ ወራሪ ዝርያዎች ጥፋት እንዳይደርስበት ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል።አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሀገር ውስጥ ብዝሀ ሕይወት የአርክቦት ፈቃድ ይሰጣል።

29) ሥልጣንና ተግባሩን ለማስፈጸም ለስራውአስፈላጊ የሆኑ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፣

30) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፡፡

31) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል።

**በህዝብ ግንኙነት ክፍል ተዘጋጀ**

**ሐምሌ 2016**